# በግሪክ ሀገር ውስጥ አለም አቀፍ ጥበቃ ለሚጠይቁ አመልካቾች ጠቃሚ እና መሰረታዊ የሆኑ መረጃዎች

አለም አቀፍ ጥበቃ ጠያቂ የሚባለው የውጭ አገር ዜጋ ወይም ዜግነት የሌለውና አለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄውን በክልላዊ ጥገኝነት ቢሮ፣ በገለልተኛ ጥገኝነት ቅርንጫፍ ቢሮ ወይም በመቀበያና በማንነት ማረጋገጫ ማዕከሎች በሚገኙ የጥገኝነት ቢሮ የሚያቀርበው ግለሰብ ነው። የአለም አቀፍ ጥበቃ ጠያቂው በዘር፣በሀይማኖት፣በዜግነት ምክኒያት እንዲሁም በተለየ የማህበር አባል በመሆኑ፣ ባለው የፖለቲካ አቋም ምክንያት፣ ወደ ትውልድ አገሩ ወይም ቀድሞ ወደ ነበረበት አገር ቢመለስ በህይወቱ ላይ፣ በተለይ የሞት ፍርድ፣ስቅላት፣ ስቃይ፣ ኢሰብአዊ ድርጊት፣ በአካሉ ላይ ጉዳት፣የሰው መዘባበቻ፣ውርደት፣ በብሄራዊ ወይም በእርስ በርስ ጦርነት ምክኒያት በህይወቱ ወይም በአካሉ ላይ ከባድ አደጋ ይደርስብኛል ብሎ በመፍራት ወደ አገሩ እንዳይመለስ ጥበቃ ሲጠይቅ ነው።

አለም አቀፍ ጥበቃ(ከለላ) አመልካች ተብሎ የሚጠራው ከሌላ የደብሊን ስምምነትን* በስራ ላይ ካዋሉ አገራት ወደ ግሪክ የተመለሰ የውጭ ዜጋንም ጭምር ነው።

## የአለም አቀፍ ጥበቃ እና ከለላ ለመጠየቅ በግሪክ ሀገር ውስጥ የት ቦታ እና እንዴት ማመልከት ይቻላል?

- የጥገኝነት ጠያቂው መቀበያ ባለስልጣን በመቅረብ ማመልከቻውን ካቀረበ በኃላ ባለሥልጣኑ ወዲያውኑ ሙሉ ምዝገባውን ያካሂዳል። ማመልከቻዎን ለመቀበል የሚመለከተው ባለስልጣን ክልላዊ የጥገኝነት ቢሮ፣ ገለልተኛ የጥገኝነት አገልግሎትና ቅርንጫፍና ተንቀሳቃሽ የጥገኝነት አገልግሎት ናቸው።

- ህጋዊ ሥርዕትን ባልጠበቀ መልኩ ግሪክ አገር የገቡ ወይም የሚኖሩ ከሆነ እንዲሁም ዜግነትዎንና ማንነትዎን የሚገልፅ ህጋዊ ሰነድ ከሌለዎት መቀበያና ማንነት ማረጋገጫ ማዕከል በመቅረብ ማዕከሉ የሚከናወነውን ሂደት ለማለፍ ይቀርባሉ። የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ማቅረብ የሚፈልጉ ከሆነ በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ የሚመለከተው ክልላዊ ጥገኝነት ቢሮ ወይም ገለልተኛ ጥገኝነት ቢሮ(የሚኖሩበት መቀበያና ማንነት ማረጋገጫ ማዕከል እንደ ገለልተኛ ጥገኝነት ሊያገለግል ይችላል) ይተለፉሉ። የአለም አቀፍ ጥገኝነት ማመልከቻዎ የምርመራ ሂደት እስኪጠናቀቅ፣ ማለትም የምርመራው ግዜ ከ25 ቀናት እስካላለፈ ድረስ በመቀበያና ማንነት ማረጋገጫ ማዕከል ውስጥ ግዴታ መቆየት ይኖርቦታል።

- የአለም አቀፍ ጥበቃ የሚጠይቀው ግለሰብ በአካል ቀርቦ ማመልከት ይኖርበታል። ከዚህም ባሻገር ማመልከቻዎን በግል የመመዝገቢያ መተግበሪያ በኩል በኤሌክትሮኒክ መልኩ ማቅረብ ይችላሉ። ግሪክ አገር አብረዎት የሚገኙ የቤተሰብ አባልዎ የጥገኝነት ጥያቄ ማቅረብ የሚፈለጉ ከሆነ ለነሱም ማመልከቻ ማቅረብ ይችላሉ። ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱት ማመልከቻውን ማቅረብ የሚፈልጉት የቤተሰብ አባልዎ አብረዎት ጥገኝነት አገልግሎት መቅረብ ይኖርባቸዋል።

1 "የደብሊን III ስምምነትን" የሚተገብሩት አገራት የሚከተሉት ናቸው: ኦስትሪያ፣ ቤልጅየም፣ ቡልጋሪያ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ዴንማርክ፣ ስዊዘርላንድ፣ ኤስቶኒያ፣ እንግሊዝ፣ አዬርላንድ፣ አይስላንድ፣ ስፔን፣ ጣልያን፣ ሳይፕረስ፣ ላትቪያ፣ ሊትዌኒያ፣ ሉዘምበርግ፣ ማልታ፣ ኖርዌይ፣ ሆላንድ፣ ሃንጋሪ፣ ፖላንድ፣ ፖርቱጋል፣ ሮማኒያ፣ ስሎቫኪያ፣ ስሎቬኒያ፣ ስዊድን፣ ቼክ ሪፖብሊክ፣ ፊንላንድ።

- ማመልከቻዎትን ሲያቀርቡ የጥገኝነት አገልግሎት ሰራተኛ ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች በሙሉ ሀቀኝነት መመለስ ይኖርብዎታል። ያቀረቡት መረጃ ሐሰት ከሆነ የጠየቁት የጥገኝነት ጥያቄ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጸእኖ ያሳድራል።
- ለአቅመ አዳም/ሔዋን ያልደረሰ ከ18 አመት በታች ከሆኑ እና በግሪክ ህግና የአፈፃፀም ደንብ መሰረት ሊንከባከብዎ ሃላፊነቱን የወሰደ አዋቂ አብሮት ከሌለ፣ ባለስልጣኑ በአስቸኳይ ለሚመለከተው የአቃቢ ህግ ማሳወቅ ይኖርበታል:: አቃቢ ህጉም ሃላፊነት የሚወስድና መብትዎን የሚያስከብር ተንከባካቢ ይመድብልዎታል። ከ15 ዓመት በታች ከሆኑ የአለም አቀፍ ጥገኝነት ማመልከቻዎን የተመደበልዎት ተንከባካቢ ማቅረብ አለበት። ከ15 ዓመት በላይ ከሆኑ የአለም አቀፍ ጥገኝነት ማመልከቻዎን በግልዎ ማቅረብ ይችላሉ። የሚመለከተው አካል እንክብካቤና ለአቅመ አዳም/ሔዋን ላልደረሱ ልጆች የተዘጋጀ የመኖሪያ ቦታ እንዲኖርዎ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።
- ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ በሚያቀርቡበት ጊዜ እርስዎም ሆነ ከ14 ዓመት በላይ የሆነ የቤተሰብ አባላትዎ ፎቶ መነሳትና የጣት አሻራ መስጠት አለበት። የጣት አሻራውም በማዕከላዊ የአውሮፓ የአሻራ መሰብሰቢያ (EURODAC) እንዲሰፍር ይደረጋል:: የደብሊን ሶስት (III) ስምምነትን በሚያከናውኑ ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች የአለም አቀፍ ጥገኝነት ያቀረቡ ከሆነ ጥገኝነት ጥያቄዎ እንዲመረመር ጥያቄውን ወደጠየቁበት አገር ይተላለፋሉ።
- በእጅዎ ያለ ዜግነትዎን የሚያረጋግጥ የጉዞ ሰንድ ወይም ከጉዳይዎ ጋር ተያያዥነት ያለው ማንነትዎን የሚያረጋግጥ ማንኛውንም ሰነድ ማስረከብ አለብዎት። ይህም ሰነድ የቤተሰቦትን እና የርሶን ማንነት፣ የትውልድ አገሮትን፣ከየት አገር እንደመጡና የቤተሰብ ዝርዝር ሰነድን ያካትታል።
- በእቃዎ ላይም ሆነ በሰውነት አካልዎ ላይ ፍተሻ ሊደረግ ይችላል:: በተጨማሪም አስፈላጊ ከሆነ የህክምና ምርመራ ሊደረግ ይችላል።
- ከጥገኝነት አገልግሎት የኢንተርቪዎ የቀን ቀጠሮ ተወስኖ ለ6 ወር የሚያገለግል የአለም አቀፍ የጥገኝነት ጠያቂ ካርድ ይረከባሉ። ይህ ካርድ ሁሌም ከእርስዎ ጋር መገኘት አለበት። ካርድዎ:
    - በፕላስቲክ መለበድ የለበትም
    - በጥሩ ሁኔታ መያዝ አለበት
    - መጥፋት የለበትም። ከጠፋ በድጋሚ ለማውጣት ከባድ ይሆናል

- የጥገኝነት ጥያቄዎን ሲያቀርቡ የሚመለከታቸው ባለስልጣናት ስለ ሂደቱ፣ ስለ መብትዎ፣ የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጠያቂው ስላለው ግዴታ እንዲሁም ደግሞ ሂደቱ በሚከናወንበት ግዜ የሚወስደውን የግዜ ገደብ በተመለከተ በሚረዱት ቋንቋ የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።
- የአስገድዶ መደፈር፣ስቃይ (ቶርቸር) ወይም ሌላ ከበድ ያለ ስቃይ የደረሰብዎት ከሆነ እርዳታ እንዲደረግልዎ ጉዳዩ ለሚመለከተው ባለስልጣን ማሳወቅ ይኖርቦታል::
- ከተባበሩት መንግስታት(OHE) ለስደተኞች የቆመው አካል ወይም የህግ፣ የሕክምናና የስነ-ልቦና እርዳታ ሊሰጡቹ ከሚችል ድርጅት ጋር መገናኘት የሚፈልጉ ከሆነ መጠየቅ ይችላሉ።
- የጥገኝነት ጥያቄ በሚጠይቁበት ወቅት የግል ጠበቃ ወይም ሌላ ራስዎ የመረጡት (በጥገኝነት አገልግሎት በኩል ሳይሆን) አማካሪ ይዘው መቅረብ ይችላል:: የጠበቃው ወይም የአማካሪው ክፍያና ወጪ የሚሸፈነው በእርስዎ ወጪ ይሆናል።
- ለኢንተርቪዎ በተገቢው መልኩ መዘጋጀት እንዲችሉና ስለጥገኝነት ሂደቱ በተመልከተ የጠበቃ ወይም የሌላ አማካሪ እርዳታ የመጠየቅ ፍላጎቱ ካልዎት አጠር ያለ ግዜ ሊሰጥዎ ይቻላል።
- በማንኛውም ሁኔታ ኢንተርቪዎ በሚደረግበት ጊዜ ከባድ ምክኒያት ካልዎ ኢንተርቪዎን የሚያደርገውን

የጥገኝነት ሰራተኛም ሆነ የአስተርጓሚውን ጾታ መምረጥ ይችላሉ። ይህ ጥያቄ ተቀባይነቱ በጥገኝነት አገልግሎቱ ይወሰናል። ሁኔታዎች ከተመቻቹ ደግሞ ፍላጎትዎን ያሟላል::

- ለአቅመ አዳም/ሔዋን ያልደረሱ ከሆኑ በወኪልዎ(ተንከባካቢዎ) በኩል ስለ ኢንተርቪዎ ማወቅ ይችላሉ። ወኪልዎም(ተንከባካቢዎ) ኢንተርቪዎ በሚደረግበት ቀን አብርዎት መገኘት ይችላል። በተጨማሪ ባለስልጣኑ ትክክለኛ እድሜዎን ለማወቅ የህክምና ምርመራ ሊያደርግ ይችላል። ይህም ሂደት የሚፈፀመው እርስዎ ወይም ወኪልዎ ከተነገርዎትና ከተስማሙ በኃላ ነው።

**የአለም አቀፍ ጥበቃ ጥያቄዎን ሲተውና ጥገኝነት አገልግሎቱ የጉዳዮ ሂደት እንዳይቀጥል የሚፈልጉ ሲመስለው (እርስዎ በሌሉበት) ጥያቄዎን ስለ መሻር በተመለከተ:-**

ጥገኝነት ጥያቄ ካቀረቡ በኋላ በፈለጉት ጊዜ ጥያቄዎን መሰረዝ ይችላሉ። ጥገኝነት ጥያቄዎን ለመሰረዝ ክልላዊ ጥገኝነት ቢሮ በአካል በመቅረብ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርብዎታል። ጥያቄዎ እንዳይመረመር ካሳወቁ በኃላ አገልግሎቱ ጉዳይዎን መመርመር ያቆማል። ምንም አይነት የመኖርያ ፈቃድ በእጅዎ ከሌልዎ ደግሞ አገሪቷን ለቀው መውጣት ይኖርብዎታል።
የጥገኝነት አገልግሎቱ የጥገኝነት ማመልከቻዎ ሂደት እንዲቀጥል እንደማይፈልጉ አድርጎ ሊወስድ( አመልካቹ በሌለበት)። ሂደቱ እንዲቋርጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ) ጥገኝነት ጥያቄዎን የሚመለከቱ አስፈላጊ መረጃዎች ሲጠየቁ ካልሰጡ

ለ) አገልግሎቱ ግላዊ ኢንተርቪዎን በወሰነበት ቀን ካልቀርቡ

ሐ) ከመቀበያ ተቋሙ ጠፍተው ከወጡ

መ) በእስር ሳሉ ከፖሊስ የተጣለብዎትን ግዴታ ካልተወጡ

ሰ) ባለስልጣኑ የሰጥዎትን የመኖሪያ ቤት ለሚመለከተው አካል ሳያሳውቁ ለቀው ከሄዱ

ረ) የጥገኝነት አገልግሎቱን ፍቃድ ሳይጠይቁ አገር ለቀው ከሄዱ

ሠ) የመኖሪያ አድራሻዎን ወይም ስልክ ቁጥርዎን መለወጥዎን በአስችኳይ ለጥገኝነት ቢሮ ካላሳወቁ

ሸ) የጥገኝነት አገልግሎቱ ጥሪ አድርግዎለት ካልቀረቡ

ቀ) በእጅዎ ያለን ወይም ማቅረብ የሚገበዎትንና ማቅረብ የሚችሉትን ሰነድ ካላቀረቡ

በ) የተሰጠዎን ጊዜያዊ ካርድ ግፋ ቢል እስከ ሚቃጠልበት ቀን ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን ድረስ ቀርበው ካላሳደሱ

ተ) የተሰጥዎትን ግዴታ ሳያከብሩ ቀርተው ከሚመለከተው ባለስልጣን ጋር ጉዳዩን ለመፍታት ካልተባበሩ

ቸ) የአለም አቀፍ ጥበቃ ጥያቄዎ ምርመራ ያለ ምንም እንከን እንዲመረመር ወደ መቀበያና የማንነት ማረጋገጫ ማዕከል ቀርበው በማዕከሉ የሚደረገውን ሂደት እንዲጠናቀቅ የወጣውን ውሳኔ እንዲከናወን ካልተባበሩ። ውሳኔ አውጪው ባለስልጣን ያቀረቡትን የጥገኝነት ጥያቄ እንዲቋረጥ የሚፈልጉ ከመሰለው ያለውን መረጃ መሰረት በማድረግ እርስዎ በሌሉበት ውሳኔ ያወጣል። መረጃዎ መሰረተቢስ ከሆነ ደግሞ ጥያቄዎን ውድቅ ያደርጋል። አገልግሎቱ ውድቅ ውሳኔ ካወጣ በኃላ የይግባኝ ባለስልጣን በመቅረብ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አልዎት።

የጥገኝነት አገልግሎቱ ጥያቄዎትን ለመመርመር የሚያስችል በቂ መርጃ ከሌለው ምርመራው እንዲቆም ውሳኔ ያወጣል። የጥገኝነት ጥያቄዎ ምርመራ እንዲቋረጥ ውሳኔ ከወጣ ወደ አገርዎ የመለስ ሂደቱ ይተገበራል። የተቋረጠው ምርመራ እንዲቀጥል ወይም እንደ አዲስ የጥገኝነት ጥያቄ ማቅረብ ከፈለጉ የምርመራው መቋረጡ ውሳኔ በወጣ በዘጠኝ (9) ወር ውስጥ መጠየቅ ይችላሉ። ይግባኙን የመጠየቅ መብት ያልዎት ለአንድ

ግዜ ብቻ ነው።

**የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጥበቃ ጥያቄ እና ሂደቱ:-**

- የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄ ሂደት የሚቀርበው በነፃና ያለምንም ክፍያ ነው። ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ ወይም ዜግነት አልባ የሆነ አለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄ የማቅረብ መብት አለው።
- ሙሉ የጥገኝነት ጥያቄዎ ምዝገባ በሚደረግበት ግዜ የሚከተሉት መረጃዎች ይካተታሉ: የማንነትዎ መረጃ፣ ከየት አገር እንደሆኑ፣ የእናትና የአባትዎ ስም፣ የባለቤትዎና የልጆችዎ ስም፣ የኢሜል አድራሻ ካልዎት፣ የባዮሜትሪክ ገፅታዎች፣ አለም አቀፍ ጥገኝነት የሚጠይቁበትን ሙሉ ምክኒያት፣ የመኖርያ አድራሻዎ፣ የጥገኝነት ጥያቄዎ የሚመረመርብትን ቋንቋና መመደብ የሚፈልጉት ተወካይ ካለ።
- በማንኛውም ምክኒያት የጥገኝነት ጥያቄዎን ሲያቀርቡ ምዝገባዎ ካልተደረገ ቢያንስ በ(3) የሥራ ቀን ውስጥ አነስተኛ አስፈላጊ መረጃዎችን ያካተተ በተለይ ጥያቄዎ የሚመረመርበትን ቋንቋ ያካተተ ምዝገባ መደረግ አለበት። በመቀጠል በሚነገርዎ የተወሰነ ቀን ሙሉ ምዝገባዎ ይደረጋል። ሙሉ ምዝገባዎን እስከሚያደርጉ ድረስ መረጃዎና ፎቶግራፍዎ ያለበት ሰነድ ይሰጥዎታል። ይህንንም ሰነድ የመጨረሻውን ምዝገባ ለማድረግ አገልግሎቱ ሲቀርቡ ካስረከቡ በኃላ በጥገኝነት ጠያቂ ካርድ ይተካልዎታል።
- የጥገኝነት ጥያቄዎን ሲያቀርቡ ከጥገኝነት አገልግሎቱ ሰራተኞች ጋር በሚረዱት ቋንቋ ሊያግባባዎ የሚረዳ አስተርጓሚ ይኖራል።
- ከጥገኝነት ጥያቄ ምርመራ ሂደት ጋር ግንኙነት ያለው፣ የእርስዎንና የቤተሰብዎን አባላት ማንነት ማረጋገጫ፣ የመጡበትን አገር እንዲሁም ደግሞ ከቤተሰብ ዝርዝር ሁኔታን በተመልከተ የሚያረጋግጥ በእጅዎ ያለ የጉዞ ሰነድ (ፓስፖርት) ወይም ማንኛውም ሌላ አይነት  ሰነድ ካልዎ ማስረከብ ይኖርቦታል።

- ጥገኝነት አገልግሎቱ በሰጠዎ የቀጠሮ ቀን ቀርበው በጥገኝነት አገልግሎቱ ሰራተኛ አማካኝነት ኢንተርቪዎን ያደርጋሉ። ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ እውነተኛ መልሶች እንዲሁም ትክክለኛ እና የተሟሉ ማስረጃዎች ብቻ ማቅረብ እና ማንኛውም አይነት ከጉዳይዎ ጋር ተያያዥነት ያለው ማስረጃ ሳይደብቁ ሊያሳውቁ ይገባል። ያቀረቡት ማስረጃዎች እንዲሁም የሰጡት ቃል እውነተኛ ካልሆኑ ውሳኔው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያስከትላል።

- ኢንተርቪዎ በሚደረግበት ቀን የጥገኝነት አገልግሎቱ ሰራተኛ በዋነኛነት የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው: ስለ ማንነትዎ የሚጠቁሙ መረጃዎች፣ወደ ግሪክ አገር እንዴት እንደመጡ፣በምን ምክንያት ያሉበትን አገር ለቀው እንደመጡ፣ዜግነት የሌሎት ከሆነ እንዲሁም ወደ አገርዎ መመለስ የማይፈልጉበትን ወይም የማይችሉበትን ምክንያት።  በኢንተርቪዎ ቀን ማንኛውንም ጠቃሚ መረጃ ነው ብለው ያሉትን በመጨመር መናገር ይችላሉ።

- በኢንተርቪዎ ቀን ከጥገኝነት ሰራተኛው ጋር በቋንቋ መግባባት የማይችሉ ከሆነ አስተርጓሚ እንዲኖር ይደረጋል።

- በኢንተርቪዎ ቀን ከጠበቃዎ ጋር ወይም ከሌላ አማካሪ (ለምሳሌ የስነ ልቦና ባለሙያ ፣ ከሶሻል ወርከር ሰራተኛ ወይም ሃኪም ጋር) አብሮ መቅረብ ይችላሉ።

- በኢንተርቪዎ የሚናገሩት ማንኛውም ነገር ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ይሆናል።

- ኢንተርቪዎ ሊቀዳ ይችላል። ኢንተርቪው ካልተቀዳ ሰራተኛው ሙሉ ጥያቄና መልሱን በጽሁፍ ያሰፍራል። ይህ ሁኔታ ከተከሰተ  በአስተርጓሚው እርዳታ የተጻፈውን ካረጋገጡ እንዲሁም ስህተት ካለ እርማት እንዲደረግ ከጠየቁ በኋላ ይፈርማሉ። የቅጂውን ኮፒም ሆነ የጽሑፉን ግልባጭ

በፈለጉበት ጊዜ ጠይቀው መውሰድ ይችላሉ ።

- ከኢንተርቪዎ በኋላ የጥገኝነት አገልግሎቱ የፖለቲካ ጥገኝነት፣ድጋፋዊ ጥበቃ ባለመብትነት ይገባዋል ወይም ማመልከቻው ተቀባይነት የለውም ሲል ውሳኔ ያወጣል::
- ለአቅመ አዳም/ሔዋን ያልደረሱ ከሆኑ ስለ ኢንተርቪዎ በተንከባካቢዎ በኩል ማወቅ ይችላሉ። ተንከባካቢዎ ከአገልግሎቱ በሚቀርብለት ጥሪ መሰረት በኢንተርቪዎ ቀን እብርዎት መገኘት ይችላል። የእድሜዎትን ትክክለኛነት በተመልከተ ባለስልጣኑ ጥርጣሬ ካደረበት እድሜዎን ለማረጋገጥ የህክምና ምርመራ ሊያደርግ ይችላል። ባለስልጣኑ የህክምናውን ሂደት በተመለከተ እርስዎንም ሆነ ተንከባካቢዎን ማሳወቅና መስማማታችሁን ማረጋገጥ አለበት።
- ጥገኝነት አገልግሎቱ የጥገኝነት ጥያቄዎን ውጤት እንዲረከቡ የሚያሳውቅዎ በሰጡት አድራሻ፣ በስልክ ቁጥርዎ፣በፖስታ፣በፋክስ ወይም በኢሜል አድራሻዎ በኩል ይሆናል።
- ጥገኝነት አገልግሎቱ ውሳኔውን የሚሰጠዎ በሚረዱት ቋንቋ በአስተርጓሚ እርዳታ አማካኝነት መሆን ይኖርበታል።

**የአለም አቀፍ ጥበቃ ጠያቂ መብት እና ግዴታዎች:-**

የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጠያቂ መብቶች

በግሪክ አገር ጥገኝነት ጠያቂ ከሆኑ ከታች የተዘረዘሩት መብቶች አልዎት:

- የጥገኝነት ጥያቄዎ ምርመራ እስኪጠናቀቅ ድረስ ግሪክ አገር የመኖር መብት አልዎት። በተመሳሳይ ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ድርስ ወደ አገርዎ ሊባረሩ አይችሉም።
- በተሰጥዎ የጥገኝነት ጠያቂ ካርድዎ ላይ በተወሰነ የአገሪቱ ክፍል ብቻ እንዲንቀሳቀሱ ገደብ (ጂግራፋያዊ ገደብ)የተወሰነ መሆኑን የሚያሳይ ካልሆነ በስተቀር በአገሪቷ በነፃነት መንቀሳቀስ ይችላሉ።
- የማይሰሩ ከሆነና የለት ተለት ወጪዎን መሸፈን የማይችሉ ከሆነ አበል የመውሰድ መብት አልዎት። እንዲሁም የመጠለያ ማዕከል ወይም ሌላ አይነት የመጠለያ ቦታ (ግላዊ መኖርያ ወይም ሆቴል ከሚያቀርብ ፕሮግራም) መጠለያ ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ። የመጠለያ ጥያቄዎ ክፍት ቦታ ካለ ተቀባይነት ያገኛል።
- አለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄ አቅርበው 6ወር ካለፈ በኃላና የጥገኝነት ጠያቂ ካርድ ካልዎ በግሪክ አገር ህግ መሰረት የመስራት መብት አልዎት።
- ሰራተኛ ከሆኑ ልክ እንደ ግሪክ ዜጎች ተመሳሳይ የሆነ የደህንነት(የኢንሹራንስ) መብትና ግዴታዎች አልዎት።
- የመድኃኒትና የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ግዝያዊ የደህንነትና ቁጥር (PAAYPA) የማውጣት መብት አልዎት።
- ልጆችዎ ነፃ የመንግስት ትምህርት ማግኘት ይችላሉ።
- ለአቅመ አዳም/ሔዋን የደረሱ ከሆኑ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት የማግኘት ምብት አልዎት።
- የሙያ ሥልጠና ማግኘት ይችላሉ።
- ከ67% ያለፈ የአካል ስንኩል ከሆኑና በመቀበያ ማዕከል መኖር የማይችሉ ከሆነ የአካል ስንኩልና አበል የመቀበል መብት አልዎ።

**የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጠያቂ ግዴታዎች**:

በግሪክ አገር የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጠያቂ ከሆኑ ከታች የተዘረዘሩት ግዴታዎች አልዎ:

- በከባድና የተለየ የሰብአዊ ምክኒያቶች (ለምሳሌ በከባድ የጤና ችግር ምክኒያት) በስተቀር ግሪክ አገርን ለቀው ወደ ሌላ አገር መውጣት አይችሉም። ወደ ሌላ አገር ለመጓዝ ጥገኝነት አገልግሎት የጉዞ ሰነድ

ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርቦታል። አገልግሎቱን ሳያሳውቁ ከግሪክ አገር ከወጡ ያቀረቡት የጥገኝነት ጥበቃ ጥያቄ ምርመራ ይቋረጣል።

- የጥገኝነት ጥያቄዎ ምርመራ እስኪጠናቀቅ ድረስ ግሪክ አገር መገኘት ይኖርቦታል።

- ከአገርዎ ቤተሰቦችዎን ማምጣት አይችሉም።

- ማንኛውም አይነት የጥገኝነት ጥያቄዎን ጉዳይና የማንነትዎን መረጃ ለማረጋገጥ ለሚደረግ ተግባር በተመለከተ ከግሪክ ባለስልጣን ጋር መተባበር ይኖርቦታል።

- ውሳኔ ከመቀበያ ባለስልጣን በአካል እንዲቀርቡ ጥሪ  ከሚመልከተው ባለስልጣን ጥሪ ከደረስዎ በአስቸኳይ መቅረብ ይኖርቦታል።

- የጉዞ ሰነድዎን ለአገልግሎቱ ማስረከብ አለብዎት። እንዲሁም ደግሞ ማንነትዎን ከሚያረጋግጡ መረጃ ጋር፣ ከመጡበት አገር፣ ከአገርዎ ጋርና ከቤተሰብ ዝርዝር ሁኔታ መረጃዎ ጋር ግንኙነት ያላቸውንም ማንኛውንም በእጅዎ የሚገኙ ሰነዶች ማቅረብ ይኖርቦታል።

- የመኖርያ አድራሻዎንና የመገኛ አድራሻዎን እንዲሁም በማንኛውም ሰዓት ከላይ የተጠቀሱትን አድራሻ ከለወጡ አዲሱን በአስቸኳይ ለጥገኝነት አገልግሎቱ ማሳውቅ ይኖርቦታል (አባሪ: Link 6)። የመገኛ አድራሻዎን ለመለወጥ ከፈለጉ ማመልከቻዎን በኤሌክትሮኒክ መልኩ (link የኤሌክትሮኒክ ማመልከቻዎች) ማቅረብ ይችላሉ።
- የጥገኝነት ጥያቄዎ ምርመራ ሲከናወን በማንኛውም ሂደት ላይ የሚሰጥዎን የግዜ ገደብ ማክበር ይኖርቦታል።
- የጥገኝነት ጠያቂ ካርድዎን የማለቂያ ግዜ ገደቡ ከማለቁ በፊት አገልግሎቱ በሰዓቱ ቀርበው ማሳደስ ይኖርቦታል። ቢያንስ የግዜ ገደቡ ካለቀ እስከሚቀጥለው የሥራ ቀን ድረስ ቀርበው ማሳደስ ይችላሉ።
- ከአገሪቱ መንግስት የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን የሚቀበሉ ከሆነ ያልዎትን ትክክለኛ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ማሳየት ይኖርቦታል።
- በመጠለያ ማዕከል ወይም በሌላ የመጠለያ ቦታዎች የተሰጠዎት ነፃ የመኖርያ መብት ከታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከተፈጠሩ ይቀማሉ:
  - የሚመለከተውን አካል ሳያሳውቁ የመኖርያ ማዕከሉን ለቀው ከሄዱ
  - ግላዊ መረጃዎን መለወጥዎን ሳያሳውቁ እንዲሁም የጥገኝነት ጥያቄዎን በተመለከተ መረጃ ለማቅረብና በተወሰነልዎ የኢንተርቪ ቀጠሮ ካልቀረቡ
  - በበቂ ምክኒያት በአስቸኳይ የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄ ካላቀረቡ
  - የገቢ ምንጭዎን ከደበቁና በመቀበያ ማዕከሉ የሚሰጡትን ቁሳቁሶች በኢፍትሃዊ መንገድ ጥቅም ለማግኘት ከሞከሩ።
  - የመጠለያ ማዕከሉን የአሠራር ደንብ ከጣሱ
- ከሚመልከተው አካል ጋር አብሮ የመስራት ግዴታዎን ከጣሱ። በተለይ ለጥገኝነት ጥያቄዎ ምርመራ አስፈላጊ የሆነውን ለማጣራት የሚመለከተው አካል ካልቀረቡ ወይም ካልተባበሩ። ይህም የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄዎን ምርመራ ሂደት እንከን የለሽ በሆነ መልኩ እንዳይጠናቀቅ መሰናክል ከመሆን ባሻገር የማመለካቻዎ ምርመራም ወደመቋረጥ ያመራል።

**ለጥገኝነት ጥያቄ የይግባኝና በሁለተኛ ደረጃ ጉዳይዎ እንዲመረመር ያልዎ መብቶች**

- የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻዎ ውድቅ ሆኖ ከወጣ ወይም ድጋፋዊ ጥበቃ ብቻ እንዲሰጥዎ ከተፈቀደሎዎ እርሶ ግን የፖለቲካ ጥገኝነት ይገባኛል ብለው ካሙኑ የይግባኝ ጥያቄ ወደሚመለከተው ባለስልጣን ቀርበው አቤት ማለት ይችላሉ። የይግባኝ ማመልከቻዎን በውሳኔው ላይ የተጠቀሰው ቀነ ገደብ ሳያልፍ ውሳኔውን አውጥቶ ለሰጠዎ የክልሉ የጥገኝነት ቢሮ ወይም የጥገኝነት ቅርንጫፍ ቢሮ ማቅረብ ይኖርብዎታል።
- የጥገኝነት ጥያቄ ውሳኔዎን የተቀበሉበት ክልላዊ የጥገኝነት ቢሮ (ወይም ገለልተኛ የጥገኝነት ቢሮ) ከሚኖሩበት የመጠለያ ማዕከል ራቅ ብሎ የሚገኝ ከሆነ በአቅራቢያዎ ከሚገኘው ክልላዊ ጥገኝነት ቢሮ በመቅረብ የይግባኝ ማመልከቻዎን ማቅረብ ይችላሉ። በመቀጠል ያቀረቡት የይግባኝ ጥያቄ ውሳኔዎን ወደተረከቡበት ክልላዊ ወይም ገለልተኛ የጥገኝነት ቢሮ ጥያቄዎን ባቀረቡበት ቀን በኤሌክትሮኒክ መልኩ ያስተላልፋል። የይግባኝ ማመልከቻዎ የሚቀርበው በአካል ወደ ሚመለከተው የጥገኝነት አገልግሎት በመቅረብና በጠበቃዎና በእርስዎ የተፈረመ (የይግባኝ) ሰነድ በመያዝ ነው። በእስር ላይ ወይም በማዕከል የሚገኙ ከሆነ የይግባኝ ማመልከቻዎ የሚከናወነው በእስር ቤቱ ወይም በማዕከሉ ኃላፊ በኩል መሆን አለበት። በመቀጠል ኃላፊው የይግባኝ ማመልከቻዎን በፋክስ ወይም በሌላ አይነት የኤሌክትሮኒክ መንገድ በኩል ውሳኔዎን ወደተረከቡበት ክልላዊ ወይም ገለልተኛ የጥገኝነት አገልግሎት ይልካል።
- የይግባኝ ማመልከቻ ካቀረቡ በኃላ የአለም አቀፍ የጥገኝነት ጠያቂ ካርድ ይሰጥዎታል።
- የይግባኝ ጥያቄያዎ በይግባኝ ኮሚቴ ይመረመራል። ኮሚቴው በአብዛኛውን ግዜ ጉዳይዎን የሚመረምረው ፋይልዎ ላይ ያሉትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ነው። ይግባኝዎ የሚመረመርበትን ቀን እንዲሁም የይግባኝ ኮሚቴው ግምት ውስጥ ሊያስገባው የሚፈልጉት ተጨማሪ ማስረጃ ካልዎ መቼ ይዘው መቅረብ እንደሚችሉ ይነገርዎታል።
- የይግባኝ ማመልከቻዎ በሚታይበት ቀን በአካል የይግባኝ ባለስልጣን መቅረብ ይኖርቦታል። ካልቀረቡ የይግባኝ ማመልከቻዎ ውድቅ ይሆናል።
- ይግባኝ ጠይቀው  ውጤቱን በመጠበቅ ላይ እያሉ ሂደቱን ማቋረጥ ከፈለገ ማቋረጥ ይችላሉ። ይህ የሚሆነው በአካል ማመለከቻዎን ያቀረቡበት ክልላዊ የጥገኝነት ቢሮ በመቅረብ ሂደቱ እንዲቋረጥ በጽሁፍ ሲያሳውቁ ነው። የጥገኝነት ቢሮ በጠየቁት መሰረት ጉዳይዎ እንዲቋረጥ ያደርጋል። በተጨማሪ አገሪቷ ላይ መቆየት የሚያስችል ምንም አይነት የመኖሪያ ፍቃድ ከሌልዎ አገሪቷን ለቀው መሄድ አለብዎት።
- የይግባኝ ኮሚቴው የይግባኝ ጥያቄዎ ሂደት እንዲቀጥል እንደማይፈልጉ አድርጎ ሊወስድ (አመልካቹ በሌለበት) ይችላል።  ሂደቱን ለማቋረጥ የሚያስችሉት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1) ከማመልከቻዎ ጋር ግንኙነትና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በተመለከተ ባለስልጣኑ ሲጠይቅዎ ካልሰጡ

2) ከመቀበያ እና መመዝገቢያ ተቋሙ (ካምፕ) ጠፍተው ወይም ሳያሳውቁ ከወጡ

3) በእስር ላይ እያሉ ከፖሊስ የተጣለቦትን ግዴታ ካልተወጡ

4) ባለስልጣኑ የሰጥዎትን የመኖሪያ ቦታ ለሚመለከተው ክፍል ሳያሳውቁ ለቀው ከሄዱ

5) ከጥገኝነት ቢሮ ፍቃድ ሳይጠይቁ አገር ለቀው ከሄዱ

6) የመኖሪያ አድራሻዎን ወይም የመገኛ አድራሻዎን መቀየርዎን ለጥገኝነት ቢሮ በአስቸኳይ ካላሳወቁ

7) ከይግባኝ  ባለስልጣን ጥሪ ደርስዎት ካልቀረቡ

8) የተሰጠዎን ካርድ ለማሳደስ ቢያንስ ከተቃጠለበት ቀን ቀጥሎ እስካለው የስራ ቀን ድረስ ካልሄዱ ወይም

9) በእጅዎ በእርግጠንነት ያለን ወይም ማቅረብ የሚችሉትንና ያለብዎን ሰነዶች ካላቀረቡ

- የይግባኝ ኮሚቴው እንደገና ኢንተርቪ ማድረግ እንዳለብዎ ካመነ ኢንተርቪዎ ከሚደረግበት ቀን ግፋ ቢል ከአስር(10) የስራ ቀናት በፊት እንዲቀርቡ ያሳውቆታል:: በእለቱ

ጠበቃ ወይም ሌላ አማካሪ ይዘው የመቅረብ መብት አልዎ።

- የይግባኝ ኮሚቴው የፖለቲካ ጥገኝነት ጥበቃ ወይም ድጋፋዊ ጥበቃ ባለመብትነት ይገባዋል ወይም ይግባኙ ተቀባይነት የለውም ሲል ውሳኔ ያወጣል::
- የይግባኝ ኮሚቴው ውሳኔ የሚሰጥዎ ከዚህ በፊት ከጥገኝነት አገልግሎት ውሳኔ በተረከቡበት አይነት መልኩ ይሆናል።
- የጉዳይዎን ሁኔታ መሰረት በማድረግ የይግባኝ ማመልከቻዎን ውሳኔ ከአስራ አምስት(15) ቀን እስከ ሦስት(3) ወር ባለው የግዜ ገደብ ውስጥ ያወጣል።
- የይግባኝ ጥያቄዎ ተቀባይነት ካላገኘ ወይም ድጋፋዊ ጥበቃ ከተሰጥዎትና የፖለቲካ ጥገኛ ይገባኛል ብለው ካሙኑ በአቅራቢያዎ ከሚገኝ የሚመልከተው የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አስተዳደር ውሳኔው እንዲሰረዝልዎ መጠየቅ ይችላሉ። ይህንንም ሂደት ውሳኔው ከተሰጥዎ ከሚቀጥለው ቀን ጀምሮ በሰላሣ (30) ቀን ውስጥ ማድረግ ይችላሉ። ውሳኔው እንዲሰረዝ ጥያቄ ካቀረቡና የይግባኝ ጥያቄዎ ውድቅ ሆኖ ከወጣ ከግሪክ አገር ያለመባረር ከለላ ሊሆን አይችልም።

## በእስር ላይ ያሉ የአለም አቀፍ ጥበቃ ጠያቂዎችን በተመለከተ

- በእስር ላይ ወይም በመቀበያና በማንነት ማረጋገጫ ማዕከል (መማማማ) ውስጥ የሚገኙ ከሆነና የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄ ማቅረብ የሚፈልጉ ከሆነ የእስር ቤቱ ወይም የመቀበያና የማንነት ማረጋገጫ ማዕከሉ ባለስልጣን ምዝገባዎ እንዲደረግ ለጥገኝነት አገልግሎቱ ያሳውቃል።
- የጥገኝነት ጥያቄዎ ምዝገባ በሚደረግበት ቀን በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ ክልላዊ የጥገኝነት ቢሮ ወይም በሚገኙበት የጥገኝነት አገልግሎት ቅርንጫፍ ቢሮ በፖሊስ ታጅበው ምዝገባዎ ይከናወናል።
- የጥገኝነት ምዝገባዎ በሚረዱት የአስተርጓሚ እርዳታ አማካኝነት ይደረጋል። የጥገኝነት አገልግሎቱ ሰራተኛም ሂደቱን በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃ ሁላ ያሳውቆታል።
- ማንነትዎን የሚያረጋግጡ ሰነዶች ለምሳሌ ፓስፖርት ወይም ከጉዳዮ ጋር ግኙኝነት ያላቸውን ሌላ አይነት ሰነዶች ካልዎ ይዘው መቅረብ ይኖርቦታል። የጥገኝነት ምዝገባዎን በሚያደርጉበት ቀን ፎቶና የጣት አሻራዎ ይነሳል።
- ምዝገባዎን ካደረጉ በኃላ አለም አቀፍ ጥገኝነት ጠያቂ በሚሰጠው ካርድ ፋንታ ኢንተርቪዎ ለማድረግ መቅረብ ያለቦትን ቀን የተፃፈበት ሰነድ ይሰጥዎታል።
- የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄ ሲያቀረቡ በእስር ላይ የሚገኙት በወንጀል ምክኒያት ከሆነ የተውሰነቦትን ቅጣት እስኪያጠናቅቁ ድረስ በእስር ላይ ይውላሉ።
- የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄ ሲያቀርቡ በእስር ላይ የሚገኙበት ምክኒያት ወደ ግሪክ አገር በህገ ወጥ መልኩ ስለገቡ ወይም ከግሪክ አገር እስኪባረሩ ድረስ ከሆነ ፖሊስ ከታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች እስኪመረምር ድረስ በእስር ላይ ሊቆዩ ይችላሉ:

ሀ) ትክክለኛ የማንነትዎ ወይም  የዜግነትዎ መረጃ እስኪጣራ ድረስ

ለ) ከጥገኝነት ማመልከቻዎ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መረጃዎች ማጣራት ካስፈልገና በሌላ አይነት መልኩ ለማጣራት አዳጋች ከሆነ፣ ለምሳሌ በእስር ላይ ባይሆኑ ሊያመልጡ ይችላል የሚል ስጋት ካለ

ሐ) ጥገኝነት ጥያቄ ያቀረቡት ከአገር እንዳይባረሩ ወይም እንዲባረሩ የሚወጣውን ውሳኔ እንዲዘገይ ለመከላከል ፖሊስ መረታዋ ምክንያቶች አሉ ብሎ ካሰበ

መ) ለብሄራዊ ደህንነት ወይም ለህዝብ ስርዓት አደጋ የሚፈጥሩ ከሆነ።

ሰ) በአውሮፓ የደንብ ቁጥር 604/2013 ትርጓሜ መሰረት ሊያመልጡ የሚችሉበት ከባድ ስጋት ካለና በዚህም ምክኒያት የመጓጓዝዎ ሂደት  ከላይ በተጠቀሰው ደንብ መሰረት በደህንነት እንዳይከናወን የሚፈጠር አደጋ

ካለ።

- የእስራትዎን ምክኒያት ግምት ውስጥ በማስገባት ከሃምሳ(50) ቀናት እስከ አስራ ስምንት(18) ወራት ድረስ በእስር ላይ ሊቆዩ ይችላሉ ። እስራትዎን በተመለከተ የሚወስነው የፖሊስ ጣቢያው ሃላፊ ሲሆን የታሰሩበትንም ምክኒያት በዝርዝር ማስረዳት ይኖርበታል።
- በታሰሩበት ክልል የሚመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ወይም ሀላፊ ፊት በመቅረብ የእስራትዎን ውሳኔ አለመስማማትዎን የመግለጽ መብት አልዎት።
- የጥገኝነት ጥያቄዎን ማመልከቻ ማቅረብ የማይፈልጉ ከሆነ ለሚመለከተው የጥገኝነት አገልግሎት በአካል ቀርበው ማሳወቅ ይኖርበታል። ጥገኝነት ጥያቄዎን ለማቅረብ እራሱን የቻለ የጥገኝነት ቅርንጫፍ ቢሮ በታሰሩበት ቦታ ውስጥ ወይም በአቅራቢያዎ የማይገኝ ከሆነ በአቅራቢያዎ ወደሚገኘው ክልላዊ የጥገኝነት ቢሮ በፖሊስ ታጅበው መቅርብ ይኖርቦታል።
- በእስር ወይም በመቀበያና ማንነት ማረጋገጫ ማዕከል የሚኖሩ ከሆነ የአለም አቀፍ ጠያቂ ካርድ የሚሰጥዎ የጥገኝነት ጥያቄዎ ምርመራ በእንጥልጥል ላይ እያለ ከእስር ከተለቀቁ ወይም በመቀበያና ማንነት ማረጋገጫ ማዕከሉ ውስጥ የሚደረገው ሂደት ከተጠናቀቀ በኃላ ነው። የጥገኝነት ጠያቂ ካርድ ካልተረከቡ ለመረከብና የመገኛ አድራሻዎን ለማሳወቅ የሚመለከተው ክልላዊ ጥገኝነት ቢሮ በአስቸኳይ መቅረብ ይኖርቦታል።
- የጥገኝነት ጥያቄዎ ውሳኔ ከሚመለከተዉ የጥገኝነት አገልግሎት ሰራተኛ ወይም ካሉበት የማቆያ ወይም የማዕከሉ ባለስልጣን ኃላፊ ይሰጥዎታል።
- የጥገኝነት ጥያቄዎ ተቀባይነት ያላገኘ ከሆነ ከሚመለከተው የጥገኝነት አገልግሎት ሰራተኛ በአካል በመቅረብ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ።
- ካሉበት የማቆያ ማዕከል ውስጥ ወይም በአቅራቢያዎ እራሱን የቻለ የጥገኝነት ቅርንጫፍ ቢሮ አገልግሎት የማያቀርብ ከሆነ ወይንም ደግሞ ከሌለ በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ ክልላዊ ጥገኝነት ቢሮ በፖሊስ ታጅበው መቅረብ ይኖርቦታል።
- የሚኖሩት በመጠለያ ማዕከል ከሆነና የጥገኝነት ጥያቄዎን ውሳኔ ያወጣው ክልላዊ ጥገኝነት ቢሮ ከሚኖሩበት ማዕከል ራቅ ያለ ከሆነ ይግባኝዎን አቅራቢዎ ከሚገኝ ክልላዊ ጥገኝነት ቢሮ ወይም ለሚኖሩበት የማዕከሉ ሃላፊ ማቅረብ ይችላል።
- የጥገኝነት ጥያቄዎ ውሳኔ ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ እስራትዎን የሚሰርዝ ውሳኔ ይወጣል። ከእስር በሚለቀቁበት ቀን አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ይሰጥዎታል። በመቀጠል የመኖርያ አድራሻዎንና የመገኛ መረጃዎን በአስቸኳይ ወደ ሚመለከተው ክልላዊ ጥገኝነት ቢሮ በአካል በመቅረብ ማሳወቅ ይኖርቦታል።

**እንደ አዲስ የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻ**

ከፖሊስ ጣቢያ፣ ከጥገኝነት አገልግሎት ከይግባኝ ባለስልጣን የዓለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄዎ ተቀባይነት ሳያገኝ ወይም በመጀመሪያ ያቀረቡትን የዓለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄ ሲተውትና እንደ አዲስ ጥገኝነት ሲጠይቁ እንደ አዲስ የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻ ይባላል። ጥገኝነት አገልግሎት እንደ አዲስ የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻ ማቅረብ ከፈለጉ ከግሪክ ፖሊስ ጣቢያ ወይም ከጥገኝነት አገልግሎት ለመጨረሻ ግዜ የወጣ ውድቅ የሆነ የጥገኝነት ጥያቄ ውሳኔ እና የዓለም አቀፍ ጥገኝነት (ከለላ) ጥያቄ የሚያቀርቡበት አዲስ ምክንያቶች መኖር አለበት።

ከመኖርያዎ በአቅራብያ ከሚገኘው ክልላዊ ጥገኝነት ቢሮ ወይም እራሱን የቻለ የጥገኝነት ቅርንጫፍ ቢሮ የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻዎንና እንደ አዲስ የተከሰቱ መረጃዎችን ማቅረብ ይኖርቦታል። እንደ አዲስ የጥገኝነት ጥያቄውን ማመልከቻ ካቀረቡ በኋላ የዓለም አቀፍ ጥገኝነት ጠያቂ ካርድ አይሰጦትም። የጥገኝነት አገልግሎቱ የሚያቀርቡትን አዲስ መረጃ በመመርመር ላቀረቡት የዓለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄ አስፈላጊ መሆን አለመሆናቸውን ይወስናል። የጥገኝነት ጠያቂ ካርድ የሚሰጥዎ እንደ አዲስ ያቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄ ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ ብቻ ነው። እንዲሁም ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካገኘ በኃላ የጥገኝነት አገልግሎቱ ያቀረቡትን የማመልከቻ ምርመራ ማድረግ ይቀጥላል።

የጥገኝነት አገልግሎቱ እንደ አዲስ ያቀረቡትን የጥገኝነት ማመልከቻ ውድቅ ካደረገው የይግባኝ ባለስልጣን በመቅረብ የተሰጥዎ የውሳኔ ወረቀት ላይ በሚጠቅሰው የቀን ገደብ ውስጥ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ።

ለሁለተኛ ጊዜ እንደ አዲስ የጥገኝነት ማመልከቻ ካቀረቡ ማመልከቻዎ በሚመረምርበት ግዜ ወደ ሀገርዎ ላለመባረር/ላለመመለስ ከለላ አይኖረዎትም።

ወደየጥገኝነት**መ/ቤት**ሲገቡ የጦር መሳሪያ፣ስለታማ የሆኑ እቃዎች ወይም ሌሎች ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ፣ ሊፈነዱ የሚችሉ ወይም በቀላሉ ተቀጣጣይ የሆኑ፣ ኬሚካልነት እንዲሁም አሲድነት ያላቸው ነገሮች ይዞ መግባት ክልክል መሆኑንል ልናሳውቅ እንወዳለን።
በተጨማሪምከትንሽቦርሳወይምሳምሶናይትበቀርሻንጣምሆነትልቅቦርሳመያዝክልክልነው። የሞባይል ስልክ መጠቀም የሚቻለው ከመ/ቤቱ ውጭ ባለው ቦታ ብቻ ነው። በመጨረሻ ቪዲዮ መቅዳትእናፎቶመነሳትበመ/ቤቱውስጥምሆነውጪየተከለከለነው።